# በተፈጥሮ ስለሚከሰት የከንፈርና የላንቃ ክፍተት በተመለከተ ለወላጆች የተዘጋጀ አጭር መልዕክት

ከፓናሶኒክ NPO የአፍሪካ ድጋፍ ፈንድ በተገኘ ገንዘብ በጃፓን የከንፈርና የላንቃ ክፍተት ፋውንዴሽን የተዘጋጀ

እኤአ 2017 ዓም

- የከንፈርና የላንቃ ክፍተት በተፈጥሮ ከውልደት በፊት የሚከሰት ችግር ነው::
- የከንፈርና የላንቃ ክፍተት በማንኛውም ህጻን ላይ ሊከሰት ይችላል::
- የከንፈርና የላንቃ ክፍተት ሁለት ሰዓት በማይሞላ የቀዶ ጥገና ህክምና ሊስተካከል ወይም ሊጠገን ይችላል::
- ልጅዎት የከንፈርና የላንቃ ክፍተት ካለበት እባክዎን የህክምና ባለሙያ ያማክሩ::
- በከንፈርና የላንቃ ክፍተት ምክኒያት ቦታቸውን ሳይጠብቁ የበቀሉ ጥርሶች በህክምና ይስተካከላሉ:: ይህ ጥርሶችን ለማስተካከል የሚደረገው ህክምና ረጅም ጊዜ ስለሚወስድ እስከ መጨረሻው ድረስ ሳያቋርጡ መከታተል ይገባዎታል::
- በከንፈርና የላንቃ ክፍተት ምክኒያት የልጆች የመናገር ችሎታ ሊዘገይ ወይም ሊጎዳ ይችላል:: በመሆኑም የከንፈርና የላንቃ ክፍተት ያለባቸውን ልጆች ሁሉ በጊዜው በትክክለኛው የንግግርና የቋንቋ ፓቶሎጂስት ባለሙያ

እንዲመረመሩ ማድረግ ይገባል::የተሟላ የንግግር ችሎታ ምርመራ ማድረግ የሚቻለው የከንፈርና የላንቃ ክፍተት ያለበት ልጅ አራት ዓመት ሲሞላው ብቻ ነው::

- የከንፈርና የላንቃ ክፍተት ያለባቸው ልጆች የጆሮ ህመም እና የመስማት ችግር ሊያጋጥማቸው ይችላል:: የከንፈርና የላንቃ ክፍተት ያለበትን ልጅ የመስማት ችሎታ ለማሻሻል አግባብ ባለው የህክምና ባለሙያ ተከታታይ የመስማት ችሎታ ምርመራ ሊደረግለት ይገባል::

- የከንፈርና የላንቃ ክፍተት በቀላሉ በህክምና ሊስተካከል የሚችል ችግር ሆኖ ሳለ በቅድመ ወሊድ ምርመራ ጽንሱ ችግሩ ያለበት መሆኑ ሲታወቅ ወዲያውኑ ውርጃ ይፈጸምበታል:: እባክሽን የከንፈርና የላንቃ ክፍተት ያለበት ቢሆንም የራስሽን ልጅ በውርጃ መግደልን አታስቢ::

- የከንፈርና የላንቃ ክፍተት ያላባቸው ልጆች ከተወለዱ በኋላም የግድያ ተግባር ይፈጸምባቸዋል::

- እባክሽን የወለድሽው ልጅ የከንፈርና የላንቃ ክፍተት ያለበት ቢሆንም ችግሩ በቀላሉ በህክምና የሚስተካከል በመሆኑ የራስሽን ልጅ ለመግደል አታስቢ::

- ❖ የከንፈርና የላንቃ ክፍተት ያለባቸውን ልጆች እና ወላጆቻቸውን ለመደገፍ የሚሰሩ በርካት መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ይገኛሉ::
- ❖ ስለሆነም የከንፈርና የላንቃ ክፍተት ችግርን እና ተያያዥ ጉዳዮችን በሚመለከት የህክምና ባለሙያዎችን ያማክሩ::
- ❖ የከንፈርና የላንቃ ክፍተትን ጨምሮ ከልዩነት ጋር የሚወለዱ ህጻናት በጤንነት እንዲያድጉ እንመኛለን::